# ምዕራፍ ሁለት ፡

## 2.1 ሥርዓተ ልመት

የሙከራ ጥያቄ አንድ

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. ምግብ ጥቃቅን ወደ ሆኑና በቀላሉ ወደ ደም ውስጥ ሊሰርጉ ወደሚችሉበት ደረጃ የመቀየር ሂደት ምን ይባላል ?

ሀ) ስርዓተ ልመት ለ) ስርዓተ ስርገት

ሐ) ሬክተም መ) ሀ እና ለ

2. ከሚከተሉት ውስጥ የምግብ መተላለፊያ ቱቦ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አፍ፣ ለ) ጉሮሮ፣ ሐ) ጨጓራ፣ መ) ትንሹ አንጀት

ሰ) ሬብና ፊንጢጣ ረ) መልስ የለም

3. የምግብ መተላለፊያ ቱቦ ከሆኑት አካላት ውስጥ የምግብ መፈጨት የማይከናወንባቸው የትኛው ነው?

ሀ) አፍ፣ ለ) ጨጓራና ሐ) ትንሹ አንጀት መ) ሬብና ፊንጢጣ

LIVEWORKSHEETS

4. የምግብ መፈጨት የሚጀምርበት የሥርዓተ ልመት አካል የትኛው አካል ነው ?

ሀ) ጨጓራ　　　　ለ) አፍ

ሐ) ትንሹ አንጀት　　　　መ) ትልቁ አንጀት

5. ከሚከተሉት ጨጓራ ውስጥ የምግብ ልመት እንዲፋጠን የሚያደርጉት የትኞቹ ናቸው

ሀ) ዝልግልግ ፈሳሽ　　　　ለ) ሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ

ሐ) ኢንዛይሞች　　　　መ) ሀ እና ሐ

6. ከሚከተሉት ውስጥ የጨጓራ ግድግዳ በኢንዛይሞች እንዳይፈጭና በሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ እንዳይጎዳ የሚከላከለው የቱ ነው ?

ሀ) ንፍጥ መሳይ ወፍራም ዝልግልግ ፈሳሽ　　　　ለ) በጨጓራ ውስጥ ያሉ ሚነራሎች

ሐ) በጨጓራ የሚመረት ኬሚካል　　　　መ) ሀ እና ለ

7. ................................ ከምግብ ጋር አብሮ ወደ ጨጓራችን የሚገቡ ጀርሞችን ለመግደል ያገለግላል፣

ሀ) ንፍጥ መሳይ ወፍራም ዝልግልግ ፈሳሽ　　　　ለ) ሃይድሮ ክሎሪክ አሲድ

ሐ) የጨጓራ ግድግዳ በኢንዛይሞች　　　　መ) ሀ እና ሐ

8. ምግብ ወደ መጨረሻ ልመት /የምግብ ንጥረ ነገሮች/ የሚለወጥበት በየትኛው የሥርዓተ ልመት ክፍል ነው ?

ሀ) ትልቁ አንጀት　　　　ለ) ሬብና ፊንጢጣ

ሐ) ትንሹ አንጀት　　　　መ) ሬብና

9. ...................... የምግብ ልመት የሚጠናቀቅበት የስርዓተ ልመት የአካል ክፍል ነው፡፡

ሀ) ትልቁ አንጀት　　　　ለ) ትንሹ አንጀት

ሐ) ጨጓራ　　　　መ) ሬብና

10. በትንሹ አንጀት ግድግዳ ላይ በሚገኙት ትንንሽ ቧንቧዎች አማካይነት ወደ ደም ስሮች የሚገባበት ሂደት ምን ይባላል ?

ሀ) ስርገት　　　　ለ) ስርዓተ ልመት　　　　ሐ) ውጣት　　　　መ) ድቀት

LIVEWORKSHEETS

11. የላመ ምግብ በቀላሉ መስረግ እንዲችል የትንሹ አንጀት ግድግዳ ላይ የሚገኙ ትናንሽ ጣት መሰል ነገሮች ምን ይባላሉ ?

ሀ) ቪላይ ለ) ሬብ ሐ) ኢንዛይሞች መ) ሬክተም

12. .................... ያልተፈጨ ምግብን በፊንጢጣ በኩል በሰገራ መልክ ወደ ውጭ ለማስወገድ ያገለግላል፡፡

ሀ) ትልቁ አንጀት ለ) ሬብና ፊንጢጣ

ሐ) ቲኒሹ አንጀት መ) ቪላይ

13. ከሚከተሉት ውስጥ ምግብ የማይፈጭበት አካል የትኛው ነው ?

ሀ) በትልቁ አንጀት ለ) ቲኒሹ አንጀት

ሐ) ጉሮሮ መ) ሀ እና ሐ

14. ........................ ውሃ በመምጠጥ ወደ ሰውነት ያሰርጋል፡፡

ሀ) በትልቁ አንጀት ለ) ቲኒሹ አንጀት

ሐ) ጨጓራ መ) ሬክተም

15. ያልተፈጨ ምግብ ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ የሚጠራቀምበት አካል የትኛው ነው ?

ሀ) በትልቁ አንጀት ለ) በሬክተም (ሬብ)

ሐ) ሬብና ፊንጢጣ መ) ሀ እና ለ

16. ጠቃሚ ያልሆኑና ወደ ደም ሰርገው ያልገቡ ቆሻሻዎች ከሰውነታችን በሰገራ መልክ በ ........................ በኩል ይወገዳል፡፡


ሀ) በፊንጢጣ ለ) በትልቁ አንጀት

ሐ) ጣፊያ መ) በሬክተም (ሬብ)

LIVEWORKSHEETS

II. የሚከተሉትን የሥር ዓተ ልመት ክፍሎች ከምስሉ ጋር በማዛመድ ትክክለኛዉን ቁጥር አስቀምጡ

1) ፊንጢጣ
2) ጉሮሮ
3) ጨጓራ
4) ጣፊያ
5) ትልቁ አንጀት
6) ትንሹ አንጀት
7) ጉበት
8) አፍ
9) የሀሞት ከረጢት



LIVEWORKSHEETS

III. በ “ሀ” ረድፍ የተቀመጡትን የኢትዮጵያ አዋሳኝ ሀገሮች በ “ለ” ረድፍ ከተቀመጡት ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የመጀመሪያውን የምግብ ቱቦ ከጨጓራ ጋር ያገናኛል | ................ ቪላይ |
| 2. ምግብ በጊዜያዊነት የሚጠራቀምበት | .................. ትልቁ አንጀት |
| 3. በጨጓራ ውስጥ የሚገኘው ንፍጥ መሳይ ወፍራም ዝልግልግ ፈሳሽ | ................... ጉሮሮ |
| 4. ምግብ ወደ መጨረሻ ልመት /የምግብ ንጥረ ነገሮች/ ይለወጣል፡ | .................. ስርዓተ ልመት |
| 5. የላመ ምግብ በቀላሉ መስረግ እንዲችል ያግዛሉ | ....................ስርገት |
| 6. ምግብ አይፈጭም፡፡ ¬ ውሃ ይመጠጥና ወደ ሰውነት ይሰርጋል | .................... ትኒሹ አንጀት |
| 7. የመጀመሪያውን የምግብ ቱቦ ከጨጓራ ጋር ያገናኛል | ..................የጨጓራ ግድግዳ እንዳይጎዳ ይከላከላል፡፡ |
| 8. ምግብ ጥቃቅን ወደ ሆኑና በቀላሉ ወደ ደም ውስጥ ሊሰርጉ ወደሚችሉበት ደረጃ የመቀየር ሂደት | ..................... ሬብ |

LIVEWORKSHEETS